# የሸሃዳን ቃል ኪዳን ለማፍረስና ኀይሉንም ለመስበር የሚጸለይ ጸሎት

*በሙሐመድ ሕይወት የተገለጡትን ትምህርቶችና የሐሰት መገዛት እክዳለሁ።*

*ሙሐመድ የአምላክ መልዕክተኛ ነው የሚለውን የውሸት እምነት አልቀበልም። እክደዋለሁም።*

*ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚለውን አነጋገር እክዳለሁ።*

*ማንኛውንም ሸሀዳን ማነብነብ አግባብ ነው ብዬ አልቀበልም። እክደዋለሁም ።*

***አል ፋቲሃ*** *አይሁዶች ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች ናቸው፣ ክርስቲያኖችም ከሀዲዎች ናቸው የሚለውን አስተምህሮ እክዳለሁ።*

*አይሁዶችን መጥላትን እክዳለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን በርዘውታል የሚባለውን አባባል አልቀበልም።*

*እግዚአብሔር ኤሁዳውያንን ጥሏቸዋል የሚለውን አመለካከት እክዳለሁ።*

*ቁርአንን ማነብነብና በሕይወቴ ላይ ስልጣን አለው የሚለውን አባባል እክዳለሁ።*

*ሙሐመድን እንደ ምሳሌ በመቁጠር የሚደረግ ማንኛውንም የሐሰት አምልኮ እክዳለሁ።*

*ሙሐመድ እግዚአብሔርን አስመልክቶ ያመጣውን የሐሰት ትምህርቶች እክዳለሁ። በቁርአን ላይ የተገለጠውን አላህ እግዚአብሔር ነው የሚለውን አባባል እክዳለሁ።*

*በተወለድኩ ጊዜ ለእስልምናና ለዘር ዘሮቼ የተሰጠሁበትን መሰጠት እክዳለሁ።*

*የሙሐመድን ምሳሌዎች ተከተል የሚለውን አስተሳሰብ እክዳለሁ። የኃይል ጥቃትን ፣ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን፣ ጥላቻን፣ በሴቶች ያለአግባብ መጠቀምን፣ ሌብነትን፣ ሙሐመድ የፈጸማቸውን ሁሉንም ኃጢአቶች እቃወማለሁ። እክዳለሁ።*

*በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ከኩነኔ ነፃ መሆነቸውን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከማንኛውም አሳፋሪ በደል ነፃ ስላወጣኝ ማንኛውንም አሳፋሪ ነገርን አልቀበልም። ደግሞም እክደዋለሁ።*

*በሙስሊሞች የሚነገር ማንኛውንም የፍርሃት ንግግር አልቀበልም ደግሞም እክደዋለሁ። በሙስሊሞች ዛቻ የተነሳ በፍርሃት ውስጥ ለወደቁት እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግላቸው፣ በሁሉም ነገራቸው በእግዚአብሔር መታመንን ምርጫቸው እንዲያደርጉ እጸልይላቸዋለሁ።*

*የሌሎችን እርግማን አልቀበልም እና እተወዋለሁ። የበረከት ሰው ለመሆን እመርጣለሁ።*

*ከጂኒ ጋር ያለኝን ግንኙነት ሁሉ ውድቅ አድርጌ እተወዋለሁ። ስለ ቀሪን የሚነገረውን የእስልምና አስተምህሮት ውድቅ አድርጌያለሁ፣ ከአጋንንት ጋር የትኛውንም ግንኙነት አቋርጣለሁ።*

*የእግዚአብሔርን ቃል ለመንገዴ ብርሃን በማድረግ በመንፈስ መመላለስን እመርጣለሁ።*

*እግዚአብሔራዊ ባልሆነው ማንኛውም ድርጊቴ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ፣ ሙሐመድንም የአላህ መልዕክተኛ ነው ብዬ በመከተሌ እግዚአብሔርን ምህረት እጠይቃለሁ።*

*ኢየሱስ ዳግመኛ ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉም ሕዝቦች የሙሐመድን ሸሪኣ እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል የሚለውን የስድብ ንግግር እቃወማለሁ ። ደግሞም እክዳለሁ።*

*ኢየሱስን ብቻ ለመከተል ምርጫዬ አድርጌአለሁ።*

*ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፣ ለኃጢአቴ በመስቀል ላይ መሞቱን፣ ለኔ ደህንነት ሲል ከሞት መነሳቱን አምናለሁ። ስለ ክርስቶስ መስቀል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። የኔን መስቀል ወስዶ እንድከተለው ስላደረገኝ፤*

*ክርስቶስ የሁሉም ጌታ መሆኑን አምናለሁ። በሰማይና በምድር ላይ ገዢ ነው። የሕይወቴ ጌታ ነው። በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ እንደሚመጣ አምናለሁ። እንድንበት ዘንድ ከሰማይ በታች የተሰጠ ከኢየሱስ ሌላ ስም እንደሌለ አምናለሁ።*

*አባቴ እግዚአብሔር አዲስን ልብ እንዲሰጠኝ ወደ ሕይወቴ እጋብዘዋለሁ። እርሱም የክርስቶስ ልብ ነው፡ በምናገረውና በማደርገው ሁሉ ይመራኝ ዘንድ፤*

*ሁሉንም የሐሰተኛ አምልኮዎች እቃወማለሁ። ህያው አምላክን ለማምለክ ማንነቴን አሰጣለሁ። አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስን።*

*አሜን።*